የፕሬስ መግለጫ

PR24/291

# የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፍጻሚ ቦርድ ለኢትዮጵያ የአራት ዓመት የ3.4 ቢሊዮን ዶላር የተራዘመ ብድር አገልግሎት አቅርቦትን አጸደቀ

## በቶሎ የሚለቀቅ

- የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ቦርድ ለኢትዮጵያ የ2.556 ቢሊዮን SDR ወይም ወደ 3.4 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚጠጋ የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦትን አጽድቋል። ይህም ውሳኔ 766.75 ሚሊዮን SDR ወይም 1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አካባቢ የሚሆን ገንዘብ ክፍያ ወዲያውኑ እንዲለቀቅ የሚያስችል ይሆናል።
- ይህ የአራት ዓመት የፋይናንስ ፓኬጅ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መፋለሶችን ለመፍታት፣ የውጪ እዳ [አከፋፈል] ዘላቂነትን በመመለስ እንዲሁም ለላቀ አካታች ለሆነ እና በግል ዘርፉ ለሚመራ እድገት መሠረትን በመጣል የመንግሥትን 'ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ' አጀንዳ የሚደግፍ ይሆናል።
- ይህ የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦት ከልማት አጋሮች እና አበዳሪዎች የሚገኝ ተጨማሪ የውጪ የገንዘብ አቅርቦትን እንደሚያፋጥን ይጠበቃል።

**ዋሺንግተን ዲሲ፤ ሐምሌ 22/2016**፡ የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፈጻሚ ቦርድ ለኢትዮጵያ የሚሆንና መጠኑም 2.556 ቢሊዮን SDR (የኮታው 850% ወይም ወደ 3.4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ) የሆነ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን መፋለስን መፍታትን እና በግል ዘርፉ ለሚመራ እድገት መሠረት መጣልን አላማው ያደረገውን የመንግሥትን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ አፈጻጸም የሚደግፍ የአራት ዓመት የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦት (ECF)[1] አጽድቋል። የአስፈጻሚ ቦርዱ ውሳኔም ኢትዮጵያ ከባላንስ ኦፍ ፓይመንት ጋር የተያያዙ ፍላጎቶቿን እንድታሟላ የሚረዳትን እንዲሁም በጀቷን የሚደግፈውን የ766.75 ሚሊዮን SDR ወይም 1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አካባቢ የሚሆን ገንዘብ ክፍያ ወዲያውኑ እንዲለቀቅ የሚያስችል ይሆናል።

በአራት ዐመቱ የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦት የሚደገፈው የመንግሥት የኢኮኖሚ ፕሮግራም የግል ዘርፉን እንቅስቃሴ የሚያነቃቃ ሁለገብ የፖሊሲ ፓኬጅን እንዲሁም የላቀ እና በይበልጥ አካታች የሆነ እድገትን ማምጣት ይቻል ዘንድ ኢኮኖሚውን ክፍት ማድረግን ኢላማው ያደረገ ነው። ማሻሻያው ተጋላጭ በሆኑ ቤተሰቦች/አባዎራዎች ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለማለዘብ ይቻል ዘንድ የማህበራዊ ሴፍቲ ኔቶችን ማጠናከርም የመንግሥት የማሻሻያ ፕሮግራም አንድ ወሳኝ ክፍለአካል ነው። ቁልፍ የሚባሉት ፖሊሲዎችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ 1) ውጪዊ ኢሚዛናዊነትን ለመፍታት እና የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለማስታገስ በገበያ ወደሚወሰን የምንዛሪ ዋጋ መሄድ፤ 2) የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፍን በማዘመን የዋጋ ግሽበትን መዋጋት፤ 3) የሀገር ውስጥ የገንዘብ ምንጮችን በማሰባብሰብ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሕዝባዊ ወጪዎች ማዋል፤ 4) ከውጪ አበዳሪዎች ጋር የሚደረጉ ወቅታዊ የእዳ ሪስትረክቸሪንግ ስምምነቶችን በመፈጸም ጭምር የእዳ አከፋፈል ዘላቂነትን መመለስ እንዲሁም 5) ወሳኝ የሆኑ የማክሮ ፋይናንሺያል ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ የመንግሥት ኢንተርፕራይዞችን የገንዘብ አቋም ማጠናከር።

"ይህ ለኢትዮጵያ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጊዜ ነው" የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ክሪስታሊና እንዳሉት። "ይህ የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦት መፅደቁ ኢትዮጵያ ለትራንስፎርሜሽን ለውጦች ያላትን ጠንካራ ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት እነዚህን ጥረቶች በመደገፍ ኢኮኖሚው ይበልጥ የተነቃቃ፣ የተረጋጋ እና ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ያሳተፈ እነንደሚሆን ይጠብቃል።"

---

[1] Extended Credit Facility ወይም የተራዘመ የብድር አገልግሎት ለረጅም ጊዜ የቆየ የባላንስ ኦፍ ፔይመንት ችግር ላለባቸው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት የመካከለኛ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ያቀርባል። የተራዘመ የብድር አገልግሎት በድህነት ቅነሳ እና እድገት ትረስት (Poverty Reduction and Growth Trust) ስር ከሚገኙ አገልግሎቶች አንዱ ነው። https://www.imf.org/en/About/Factsheets/Sheets/2023/Extended-Credit-Facility-ECF

ፕሮግራሙ ከልማት አጋሮች የሚገኝ ተጨማሪ የገንዘብ አቅርቦትን በማፋጠን እንዲሁም በመካሄድ ላይ ያለው የእዳ ሪስትረክቸሪንግ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የሚያደርግ ማዕቀፍ በመስጠት ረገድ እንደሚያግዝ ይጠበቃል።

የስራ አስፈፃሚ ቦርድን ውይይት ተከትሎ ምክትል ማኔጂንግ ዳይሬክተሯ እና ተጠባባቂ ሊቀመንበሯ አንቶኔት ሳዬህ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል፤

“ኢትዮጵያ በተከታታይ የኢኮኖሚ ግፊት፣ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ ዝቅተኛ የአለም አቀፍ ክምችት እና ዘላቂነት በሌለው ዕዳ ውስጥ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና ገጥሟታል። በምላሹም መንግስት በየተራዘመ የብድር አገልግሎትንዝግጅት የሚደገፍ አጠቃላይ የተሃድሶ ፕሮግራም ጀምሯል። ይህም ዝግጅት የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን ለመፍታት፣ የውጭ ዕዳን ዘላቂነት ወደነበረበት ለመመለስ እና ጠንካራ፣ ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ሰፊ ማሻሻያዎችን በመተግበር ላይ ያተኮረ ነው።

“የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባትን በቆራጥነት መቅረፍ፣ በገበያ የተወሰነ የዉጭ ምንዛሪ ተመን መካሄድን ጨምሮ፣ የከረንት አካውንት ገደቦችን ማስወገድ እና የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፍን ማዘመን፣ የቅርብ ጊዜ ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። ደጋፊ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣ የመንግስት በጀት ጉድለቶች በገንዘብ ህትመት ፋይናንስን ማድረግን ማስወገድ፣ የገንዘብ ፖሊሲን ማጠንከር እና የበጀት አስተዳደርን ማስተካከልን ጨምሮ የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር፣ በገበያ የተወሰነው የምንዛሪ ተመን በተሳካ ሁኔታ እንዲተገበር እና የዉጪ ምንዛሪ እጥረትን በዘላቂነት ለመፍታት እንዲያስችል ሊሆን ይገባል።

“የመንግስት ፖሊሲዎች ተጎጂዎችን ለመጠበቅ እና የማሻሻያዎቹን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ተፅእኖዎች ለመቀነስ በጥሩ ሁኔታ የተስተካከሉ ናቸው። ፖሊሲዎቹ የታለመው የገንዘብ ማስተላለፍ ፕሮግራም (PSNP) የበጀት ድልድልን በእጅጉ ይጨምራሉ። በነዳጅ እና በማዳበሪያ ላይ ጊዜያዊ ድጎማዎችን ማድረግ የበጀት ዕቅዱ አካል ናቸው, ሆኖም እነዚህ ድጎማዎቸ በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ እየጠፉ ይመጣሉ ። የማህበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን ተደራሽነት እና ተፅእኖ ማስፋት መቀጠል አስፈላጊ ነዉ።

”መንግስት የሕዝብን ፋይናንስ ዘላቂነት ለማረጋገጥ ማሻሻያዎችን እያካሄደ ነው። በዚህ ረገድ በ G20 የጋራ ማዕቀፍ ውስጥ ኦፊሴላዊ ዕዳን ጨምሮ አጠቃላይ የፋይናንስ ገቢዎችን ማሳደግ እና አጠቃላይ የውጭ ዕዳ ሽግሽግ ላይ መድረስ ወሳኝ ናቸው። በቅርቡ በተካሄደው የዐለም አቀፍ የገንዘብ የፖሊሲ ማሻሻያ ለመጀመሪያ ጊዜ 'ታማኝ የሆነ ኦፊሴላዊ አበዳሪ ሂደት' መጠቀም በ G20 የጋራ ማዕቀፍ ስር የሚገኘው ኦፊሴላዊ አበዳሪ ኮሚቴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለዚህ በየተራዘመ የብድር አገልግሎት (ECF) ለሚደገፈው ፕሮግራም የፋይናንስ ማረጋገጫዎችን እንዲያቀርብ አስችሎታል።

“ከአየር ንብረት ለውጥ እና ከግጭት በኋላ መልሶ ግንባታን ጨምሮ የህዝብ ኢንቨስትመንት አስተዳደርን ማጠናከር አስፈላጊ ነው። ግልጽነት እና የፊስካል ስጋቶች አያያዝ በተለይም ከበጀት ውጪ ከሆኑ ክፍሎች እና ትላልቅ የመንግስት ኢንተርፕራይዞች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ማጠናከር ይገባል። የታሪፍ ማስተካከያን ጨምሮ የኃይል ዘርፍ ማሻሻያዎችም አስፈላጊ ናቸው።

“በቅርብ ጊዜ የተደረገዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል ማሳደግ ዋና የማክሮ ፋይናንሺያል ተጋላጭነትን ይፈታል። የፋይናንሺያል ዘርፍ አስተዳደርን ለማሻሻል እና የፋይናንስ ጭቆናን በዘላቂነት ለመቀነስ ማሻሻያዎች አስፈላጊ ይሆናሉ። የብሔራዊ ባንክ ተልእኮ እና የአስተዳደር አደረጃጀቶችን ማጠናከር የብሔራዊ ባንክን ተዓማኒነት እና አቅም ለመገንባት ያግዛል።

"የመንግስት ታላቅ እና ሁሉን አቀፍ ሃገር በቀል መዋቅራዊ ማሻሻያ አጀንዳ በተሻለ አስተዳደር እና የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ተወዳዳሪነት እና የንግድ ሁኔታ ላይ ያተኩራል፣ የግሉ ዘርፉ የሚመራው እድገት ለማነቃቃት እና ለድህነት ቅነሳ እና የኑሮ ደረጃን ለማሳደግ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

“የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል በጎፋ ዞን በደረሰው የመሬት መደርመስ አደጋ ለሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነውን የመሬት መደርመስ አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን በመግለጽ ለመንግስት ምላሽ እና የማገገሚያ ጥረቶችን መልካሙን ይመኛል።

## አባሪ

በኢትዮጵያ ውስጥ ለበርካታ ዐሥርት ዓመታት ፈጣን እድገት እና የኑሮ መሻሻል ከተመዘገበ በኋላ የተከሰቱት ተከታታይ ችግሮች ከባድ የኢኮኖሚ ጫናዎችን በመፍጠራቸው በመንግሥት ኢንቨስትመንት የሚመራው የእድገት ሞዴል ለውጥ የማያመጣበት ወሰን ላይ ደርሷል። የሀገሪቱ መንግሥትም ማሻሻያ የማድረግን አስቸኳይነት በመገንዘብ፤ የሀገሪቱን የባላንስ ኦፍ ፔይመንት ፍላጎቶች ለማሟላት፣ በጀቱን ለመደገፍ እንዲሁም የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳን ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ የገንዘብ ድርጅቱ የአራት ዓመት የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦት እንዲያደርግለት ጠይቋል።

## የፕሮግራም አጭር መግለጫ

የኢኮኖሚ ፕሮግራሙ የግል ዘርፍ እንቅስቃሴን ለማነቃቃት የሚሆን ሁለገብ የፖሊሲ ፓኬጅ ማዘጋጀትን እንዲሁም የላቀ እና ይበልጥ አካታች የሆነ እድገት ለማምጣት ሲባል ኢኮኖሚውን በይበልጥ ክፍት ማድረግን ኢላማው ያደረገ ነው። ማሻሻያው ተጋላጭ በሆኑ ቤተሰቦች/አባዎራዎች ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለማለዘብ ይቻል ዘንድ የማህበራዊ ሴፍቲ ኔቶችን ማጠናከርም የመንግሥት የማሻሻያ ፕሮግራም አንድ ወሳኝ ክፍለአካል ነው። ቁልፍ ፖሊሲዎችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ውጫዊ ኢሚዛናዊንትን ለመፍታት እና የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለማስታገስ በገበያ ወደሚወሰን የምንዛሪ ዋጋ መሄድ፤
- የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፍን በማዘመን የዋጋ ግሽበትን መዋጋት፤
- የሀገር ውስጥ የገንዘብ ምንጮችን በማሰባብሰብ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሕዝባዊ ወጪዎች ማዋል፤
- ከውጪ አበዳሪዎች ጋር የሚደረጉ ወቅታዊ የእዳ ሪስትረክቸሪንግ ስምምነቶችን በመፈጸም ጭምር የእዳ አከፋፈል ዘላቂነትን መመለስ እንዲሁም
- ወሳኝ የሆኑ የማክሮ ፋይናንሺያል ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ የመንግሥት ኢንተርፕራይዞችን የገንዘብ አቋም ማጠናከር።

**ኢትዮጵያ፡ የተመረጡ የኢኮኖሚ አመላካቾች፤ 2021/22-2028/29**

| | 2021/22 | 2022/23 | 2023/24 | 2024/25 | 2025/26 | 2026/27 | 2027/28 | 2028/29 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Proj. | Proj. | Proj. | Proj. | Proj. | Proj. |
| **አውትፑት** | | | | | | | | |
| እውነተኛ የጂዲፒ እድገት (%) | 6.4 | 7.2 | 6.1 | 6.5 | 7.1 | 7.7 | 8.0 | 7.8 |
| **ዋጋዎች** | | | | | | | | |
| አማካኝ የዋጋ ግሽበት (%) | 33.9 | 32.5 | 26.9 | 30.1 | 16.2 | 12.2 | 10.4 | 9.6 |
| **አጠቃላይ የመንግሥት ፋይናንስ** | | | | | | | | |
| ገቢ (የጂዲፒ %) | 8.1 | 7.9 | 7.3 | 8.3 | 9.8 | 10.8 | 11.2 | 11.4 |
| ወጪ (የጂዲፒ %) | 12.7 | 10.8 | 9.4 | 11.3 | 12.4 | 13.3 | 13.6 | 13.9 |
| ፊስካል ባላንስ፤ እርዳታን ጨምሮ (የጂዲፒ%) | -4.2 | -2.6 | -1.7 | -1.7 | -2.1 | -2.0 | -2.0 | -2.0 |
| የመንግሥት እዳ (የጂዲፒ %)[2] | 48.9 | 40.2 | 34.4 | 42.9 | 38.8 | 35.8 | 33.6 | 31.5 |
| **ገንዘብ እና ብድር** | | | | | | | | |
| አጠቃላይ ገንዘብ (የ% ለውጥ) | 27.2 | 26.6 | 14.4 | 30.3 | 25.1 | 26.6 | 23.5 | 21.7 |
| የግል ዘርፍ እና የመንግሥት ኢንተርፕራዞች ብድር ((የ% ለውጥ) | 18.9 | 24.1 | 12.0 | 21.2 | 25.5 | 31.3 | 20.1 | 18.2 |
| **ባላንስ ኦፍ ፔይመንት** | | | | | | | | |
| ከረንት አካውንት (የጂዲፒ %) | -4.0 | -2.8 | -2.6 | -4.3 | -3.2 | -2.5 | -2.0 | -1.9 |
| ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት (የጂዲፒ %) | 2.6 | 2.1 | 1.6 | 2.7 | 3.2 | 2.9 | 3.0 | 3.0 |
| ሪዘርቭ (የገቢ ንግድ ባለባቸው ወራት) | 0.8 | 0.5 | 0.5 | 1.2 | 2.0 | 2.5 | 3.5 | 3.6 |
| የውጪ እዳ (የጂዲፒ %) | 24.0 | 18.1 | 15.4 | 28.3 | 26.6 | 24.5 | 22.6 | 19.8 |
| **የምንዛሪ መጠን** | | | | | | | | |
| እውነተኛ የምንዛሪ መጠን (የ% ለውጥ፣ | 10.1 | 24.0 | ... | ... | ... | ... | ... | ... |

[2] የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የረጅም ጊዜ የውጪ ሊያቢሊቲዎችን እና የኢትዮቴሌኮምን የውጪ እዳ የሚጨምር የመንግሥት እንዲሁም መንግሥት ዋስትና የሰጠባቸው እዳዎች። ተጠባቂ የእዳ ስረዛዎችን አያካትትም።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የጊዜ ገደብ፣ የዋጋ እጦት) | | | | | | | | |

- 